

# ሰላማዊ የጋራ ጥሪ

መጋቢት 10 1999

በኢትዮጵያ ያለዉ የፖለቲካ ቀውስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መውጣት ወደማንችልበት ከፍተኛ የኢኮኖሚና የማህበረሰባዊ አዘቅት ውስጥ እየከተተን ነዉ። ይህን ቀውስ በግዜ መፍታት ካልቻልን በሃገራችንና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለማሰላሰል የሚሰቀጥጥ መዘዝ መጋበዛችን አይቀርም። ይህ መዘዝ የሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ጥፋት የሚያመቻች ይሆናል። አንዱን ወገን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ፣ የአሸናፊነትና የተሸናፊነት ስርአትና ወግ የሚኖረው አይሆንም።

የታሰሩ የሕሊና እሥረኞችን በሙሉ መፍታትና በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ካሉ ሰላምና እርቅ ፈላጊ ሃይሎች ጋር መምከር ሃገራችንና ሕዝቧን ከገቡበት የፖለቲካ ቀውስ ማውጫው ብቸኛ መንገድ ነው። በስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግስት ግን በእዚህ ብቸኛ መንገድ ለመጓዝ ፈቃደኛነቱን አያሳይም።ሰላም ወዳዶች በተደጋጋሚ ያቀረቡለትን የሰላምና የእርቅ ጥሪ እስከአሁን አልሰማም ብሎ ተቀምጧል።

ስማችን ከእዚህ በታች የተዘረዘረው የፖለቲካና የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ዋና ዋና የኢትዮጵያዉያን ድህረ ገጽ አዘጋጆች ዛሬ ሃገራችን ከላችበት ችግር እንድትወጣ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወሳኝ ሚና መጨወት የሚችል ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ሃላፊነት አለበት እንለለን። አሁንም ቢሆን ሁሉም ወገኖች ፍቃዱና ፍላጎቱ ካለቸዉ የአገራችን ችግር በዉይይትና በሰላም ሊፈታ ይችላል የሚል ትልቅ እምነት ሰላለን በሥልጣን ላይ ላለዉ የኢህአዴግ መንግስት በድጋሚ የሰላም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ
የኢትዮጵያ የደቡብ ሕዝቦች ኮንግረስ
ተግባር ሊግ
የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
የኢትዮጵያ አለማቀፍ ሴቶች ማህበር
የአኙዋክ ጀስቲስ ካውንስል
የኦጋዴን ሰብዓዊ መብት ግሩፕ
የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ
የኢትዮጵያን አሜሪካን ካውንስል
የኢትዮጵያን አሜሪካን ሲቪክ አድቮከሲ
የኢትዮጵያ መምህራን ኔትዎርክ
ሚሺጋን አሶሲዬሽን ፎር ዲሞክራሲ ኢን ኢትዮጵያ
ኢትዮ ሚዲያ
ኢትዮጵያን ሪቪው
ኢትዮ ዔክስ
ኢትዮ ላየን
ማህደር
አዲስ ቮይስ
አቦጊዳ
ኢዔም ዔፍ
ኢትዮጵያን ፖሊቲክስ ብሎግ
ቃሊቲ ሬዲዮ
ሲዩዳ ኢትዮጵያ ፎረም
ቅንጅት ፎረም